የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF EDUCATION

ስ: +251 11 155 3133
ፖ. ሳ.ቁ 1367፣ አራዳ ክፍለ-ከተማ,
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
T: +251 11 155 3133
P.O. BOX 1367, ARADA SUB-CITY,
ADDIS ABABA, ETHIOPIA
www.moe.gov.et
www.facebook.com/fdremoe
@fdremoe
info@moe.gov.et

ቀን/DATE: 1 መስከረም 06 2016

ቁጥር/REF NO: 8/1256/1395/15

ለሁሉም የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች
ለሁሉም የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት
ባሉበት

ጉዳዩ፡- *በ2016 ዓ.ም የሚሰጠው የድህረ-ምረቃ ፕሮግራም የመግቢያ ፈተናን ይመለከታል፣*

የትምህርት ሚኒስቴር በየጊዜው የትምህርት ጥራትን የሚያረጋግጡና የትምህርት ውጤታማነትን የሚያሻሽሉ የተለያዩ የለውጥ አጀንዳዎችን በመቅረጽና ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል። እነዚህን የለውጥ ስራዎች ደግሞ በሁሉም የትምህርት እርከኖች ደረጃ በደረጃ ማስፈጸም ያስፈልጋል። በመሆኑም እስካሁን ድረስ በተሠሩ ጅምር የለውጥ ስራዎች የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ ተችሏል።

መንግስት በ2016 ዓ.ም ከያዛቸው የትምህርት የለውጥ ስራዎች መካከል አንዱ አገራዊ የድህረ ምረቃ ፕሮግራም የመግቢያ ፈተና እንደሚሰጥ በቁጥር 1/256/579/15 ሐምሌ 20 ቀን 2015 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ማሳወቃችን ይታወሳል ።

ስለሆነም ፈተናውን በተያዘለት እቅድና ጥራት ለማከናወን ይቻል ዘንድ ተቋማትና ተፈታኞች ሊያውቋቸው፣ ሊከተሏቸውና ሊፈጽሟቸው የሚገቡ አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተቀምጠዋል።

1. የድህረ ምረቃ የመግቢያ ፈተናው ከመስከረም 21-23/2016 ዓ.ም በሁሉም የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች በበየነ-መረብ የሚሰጥ መሆኑ፣
2. ተፈታኞች በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በተዘጋጀው Graduate Admission Testing (GAT) የመመዝገቢያ ፖርታል https://portal.aau.edu.et ከመስከረም 11 - 20 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ በበየነ መረብ ማመልከት የሚገባቸው መሆኑ፣
3. ተፈታኞች በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የመግቢያ ፈተና (GAT) የመመዝገቢያ ፖርታል ገብተው ሲያመለክቱ የመፈተኛ ጣቢያቸውን (ዩኒቨርሲቲ) እና ሌሎች መረጃዎችን በትክክል እንዲሞሉ እና መረጃው በትክክል እንዲደርሳቸው ማድረግ፣
4. ተፈታኞች ለፈተና ሲያመለክቱ ፈተናውን ለመውሰድ የሚከፈለውን ክፍያ ብር 1000.00 (አንድ ሺህ ብር) በቴሌ ብር እንዲከፍሉ ከወዲሁ የቴሌ ብር አካውንት መክፈት እንደሚገባቸው መረጃው በትክክል እንዲያውቁ ማድረግ፣
5. ተቋማት ለመማር ያመለክቱና የሚያመለክቱ አመልካቾችን በበየነ መረብ እንዲያመለክቱ እንዲሁም የፈተና ፕሮግራምና ተያያዥ መረጃዎችን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድረ ገጽና ፖርታል፣ www. aau.edu.et and https://portal.aau.edu.et ብሎም ኦፊሺያል

ቴሌግራም ቻናል፤ Testing Center IER AAU እንዲያገኙ መረጃውን በትክክል መስጠት፣

6. በየትኛውም የመፈተኛ ማዕከላት ለፈተና ለመቀመጥና ፈተናውን ለመውሰድ ተፈታኞች ፎቷቸው ያለበት Test Admission Ticket (TAT) ይዘው መገኘት ያለባቸው መሆኑ (https://portal.aau.edu.et/Web/ApplyForAdmission/TestTaker)
7. የመግቢያ ፈተናው በመላ ሀገሪቱ ባሉ የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ብቻ በበየነ መረብ የሚሰጥ በመሆኑ ከኢንተርኔት ጋር የተገናኙ ኮምፒዩተር ያላቸው የመፈተኛ ማዕከላት Safe Exam Browser (SEB) ሶፍትዌር ተጭኖባቸው Corrective and Preventive Maintenance ተደርጎላቸው እንዲሁም Power Backup እንዲኖራቸው ተደርጎ ከመውጫ ፈተና በተገኘው መልካም ተሞክሮ መሰረት አስፈላጊ ግብዓቶች ከወዲሁ ዝግጁ ማደረግ፣
8. ፈተናው በዩኒቨርሲቲዎች ኔትወርክ ብቻ የሚሰጥ በመሆኑ ይህንኑ የየዩኒቨርሲቲው አይሲቲ ዳይሬክተር ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር በመተባበር እንዲያስፈጽም መመሪያ እንዲሰጥ፤
9. ከተፈታኞች ከሚሰበሰብ ክፍያ ውስጥ ለየዩኒቨርሲቲዎቹ የሚደርሰውን ድርሻ በቴሌ ብር አማካኝነት በቀጥታ ለየዩኒቨርሲቲዎች የውስጥ ገቢ አካውንት ገቢ የሚደረግ በመሆኑ ሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች የቴሌ ብር አካውንት እንዲኖራቸው ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር በመስራትና በመክፈት፤ የውስጥ ገቢ የንግድ ባንክ አካውንታቸውን እንዲሁም ለዚህ ጉዳይ አንድ Focal Person በመምረጥ ሙሉ መረጃውን ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እስከ መስከረም 5 ቀን 2016 ዓ.ም እንዲልኩ፤
10. የመግቢያ ፈተናውን የትምህርት ሚኒስቴርና የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በጋራ የሚያስተዳድሩ እና ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር በመተባበር የሚሰጥ መሆኑ፣
11. የፈተናውን ውጤት ተፈታኞች ፈተናቸውን ሲጨርሱና በመጨረሻ መልሳቸውን ሲያስገቡ ወዲያውኑ ማየት የሚችሉ መሆኑ፣
12. ተፈታኞች የፈተናውን ውጤት የሚያሳይ ሰርተፊኬት በወረቀት (Hard Copy) አትመው መውሰድ የሚችሉ ሲሆን ለመማር በሚያመለክቱበት ተቋም ሰርተፊኬቱን ማቅረብ የሚችሉ መሆኑ፤
13. የድህረ ምረቃ ፕሮግራሞች የመግቢያ ፈተና የማለፊያ ነጥብ በትምህርት ሚኒስቴር የሚወሰን መሆኑ፣

ይህ በአገር አቀፍ ደረጃ የሚሰጠውን የመግቢያ ፈተና ያላለፉ ተማሪዎችን ተቋማት የማይቀበሉ መሆናቸው፣ ያለፉ ተማሪዎችን ሲቀበሉ ደግሞ ሌሎች የመግቢያ መስፈርቶችን የሚያረጋግጡ መሆናቸው እንዲሁም በተቋማትና በትምህርት ክፍል ደረጃ ጭምር በየተቋማቱ የውስጥ አሰራር መሰረት ሌሎች ፈተናዎች እና መመዘኛ መስፈርቶች የሚሰጡ መሆኑን እያሳወቅን፤ ከላይ በተገለጹት አቅጣጫዎች መሰረት ሁሉም አካላት የበኩላቸውን ኃላፊነትና ሚና እንዲወጡ እናሳስባለን።

ከሰላምታ ጋር

ኢባ ሚጀና (ዶ/ር)
የአካዳሚክ ጉዳዮች ዋና
ስራ አስፈፃሚ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

**ግልባጭ:**

- ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
- ለኢትዮ ቴሌኮም

**አዲስ አበባ፣**

- ለከፍተኛ ትምህርት ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ጽ/ቤት
- ለአካዳሚክ ጉዳዮች መሪ ስራ አስፈጻሚ
- ለግል ከ/ት/ተቋማት አገልግሎት ዴስክ
- ለጥራትና ብቃት ማሻሻያ ዴስክ

***ትምህርት ሚኒስቴር፤***